

## እድሜያቸው11-18 ዓመት ለሆኑት ልጆችዎ ከአደገኛ በሽታዎች የመከላከያ መንገድ የ Tdap፣ MCVና HPV ክትባት መስጠት መሆኑን ሐኪሞች ያሳስባሉ።

- አንዳንድ ለሕጻናት የሚሰጡ ክትባቶች ለሙሉ ህይወት ዘመናቸው አይቆዩም። የ 11-18 ዓመት ልጅዎ ተጠብቆ እንዲቆይ ተጨማሪ ክትባቶች ያስፈልጉታል።

- አደግ ያሉ ሕጻናትና አዋቂዎች ባንዳንድ የተወሰኑ በሽታዎች የመያዝ ዕድላቸው ከፍተኛ ስለሆነ፣ አንዳንድ ክትባቶች ለነሱ ተብለው በልዩ ይሰራሉ። ዕድሜው 11-18 የሆነው ልጅዎ እነዚህን ክትባቶች ሕጻን እያለ አላገኛቸውም።

- ልጅዎ ጤነኛ ወይም ቀለል ያለ በሽታ ተይዞ ቢሆንም ክትባቶች ከአደጋ ነጻና መፍትሔ የሚሰጡ ናቸው።

## የልጅዎን ሐኪም ስለነዚህ ክትባቶች ዛሬ ይጠይቁት!



## ዕድሜያቸው 11-18 ዓመት ለሆኑ ክትባቱ <u>በነጻ</u> ነው

የአስተዳደር ክፍያ ሊጠየቁ ይችሉ ይሆናል፣ ቢሆንም መክፈል ካልቻሉ ምሕረት ይደረግልዎታል።

**ክትባቱን አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፤**

- ሐኪምዎ፣ ነርስዎን ወይም ክሊንክዎን ያናግሩ
- Public Health – Seattle & King County ጋር በስልክ ቁጥር 206-296-4774 ይደውሉ

## ልጅዎ በየዓመቱ የጤንነት ምርመራ እንዲያደርግ በጣም አስፈላጊ ነው!

**ሐኪም፣ ነርስ ወይም ክሊኒክ ለማግኘት እርዳታ ለማግኘት የሚደውሉት ወይም የሚጎበኙት፤**

Family Health Hotline
1.800.322.2588
711 (TTY relay)
Programs of WithinReach
www.ParentHelp123.org

Public Health
Seattle & King County

GLOBALTOLOCAL

በሌላ የተለያዩ መልኮችም ቀርበዋል
Amharic
Reprinted 2013

# የ 11-18 ዕድሜ ልጅዎ ከአደገኛ በሽታዎች ተጠብቋልን?



# የመኒንጆኮካል (ማጅራት ገትር) በሽታ

## የመኒንጆኮካል በሽታ የአእምሮ ጉዳትንና ሞትን ሊያስከትል የሚችል አደገኛ በሽታ ነው።

- ከሕክምና እንክብካቤ ጋርም እንኳን፣ የህመም ምልክቶች ከታዩ በኋላ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ሞትን ሊያስከትሉ ይችላሉ።
- በሽታው ከሰው-ወደ-ሰው በጉንፋን። መሳሳም ወይም እንደ የውሃ ጠርሙስ በመሳሰሉ አፍን ሊነኩ የሚችሉ ማናቸውንም ነገሮችን በመካፈል ሊሰራጭ ይችላል።
- በሽታውን ማንኛውም ሰው ሊያገኝ ይችላል፣ ቢሆንም በቡድን ስፖርት ሲጫወቱ ወይም በዶርሞች ውስጥ ሲኖሩ፣ ተጠጋግተው የሚኖሩ ወጣቶች በበሽታው የመያስ ከፍተኛ ዕድል አላቸው።
- የመኒንጆኮካል በሽታ በጠራራ ጸሓይ ወይም ሙቀት የሚነሳ አይደለም።

## የ MCV ክትባት ከመኒንጆኮካል በሽታ ይከላከላል።

- ሐኪሞች ለልጆች 2 የ MCV ክትባት፣ ከ 11 ዕድሜ ጀምሮ እንዲሰጥ ያሳስባሉ።
- ለልጅዎ የ MCV ክትባትን ስለማስከተብ ሐኪምዎን ይጠይቁት!

# ፐርቱሲስ ("ትክትክ")

## ፐርቱሲስ ለወራት የሚቆይ ሳል ሊያስከትልና መብላትን፣ መጠጣትን ወይም ማስተንፈስን ከባድ ሊያደርግ ይችላል።

- ፐርቱሲስ በቀላሉ ከሰው-ወደ-ሰው በሳልና በማስነጠስ ይሰራጫል።
- ከፍ ያሉ ሌሎች ልጆችና አዋቂዎች አብዛኛውን ግዜ ፐርቱሲስን ለሕጻናትና ነፍሰጡር ሴቶች ያሰራጩና ሞትን ሊያስከትል ይችላል።

## የ Tdap ክትባት ከቲታነስ፣ ዲፕሴርያና ፐርቱሲስ ይከላከላል።

- ለሕጻናት የሚሰጠው የፐርቱሲስ ክትባት ለረጅም ግዜ ስለማይቆይ፣ የ Tdap ክትባት ዕድሜው 11 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆነ ለማንኛውም ሰው እንዲሰጥ ሐኪሞች ያሳስባሉ።
- ለእርስዎና ለልጆችዎ የ Tdap ክትባትን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ሐኪምዎን ይጠይቁት!



# ሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ (HPV)

## HPV የማሕጸን ነቀርሳንና የብልት ኪንታሮት መንስኤ ዋና ምክንያት ነው።

- HPV ያለባቸው ብዙዎቹ ሰዎች እንዳላቸው አያውቁም፣ ቢሆንም በግብረስጋዊ ግንኙነት ወደ ሌሎች ያሰራጩታል።
- HPV በጣም የተለመደ ነው። ቢያንስ ግማሾቹ ወንዶችና ሴቶች ሁሉ በህይወት ዘመናቸው ውስጥ በበሽታው ይያዛሉ።

## የ HPV ክትባት ከሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ በሽታንና ከማሕጸን ነቀርሳ ይከላከላል።

- የ HPV ክትባት ከማንኛውም የግብረስጋዊ ግንኙነት በፊት ከተሰጠ፣ አብዛኛውን የመከላከል ተግባሩን ይሰጣል።
- ለሴቶችና ወንዶች ሶስት ክትባቶች፣ ከ 11 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ እንዲሰጥ ሐኪሞች ያሳስባሉ።
- ለልጅዎ የ HPV ክትባትን ስለመስጠት ሐኪሙን ያናግሩት!